በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ

የፈተና ዝግጅትና አስተዳደር ዳይሬክቶሬት

የ2013ዓ.ም የ8ኛ ክፍል ከተማ አቀፍ /የመጀመሪያ ደረጃ ማጠናቀቂያ / ፈተና ላይ ገለፃ (Orientation) እና መደረግ የሚገባቸው ጥንቃቄዎች

ሰኔ/2013ዓ.ም

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ 2013 ዓ.ም የ8ኛ ክፍል ከተማ አቀፍ

(1ኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ ሰርተፍኬት)ፈተና መስጫ ጊዜ ሰሌዳ

BIIROO BARNOOTA BULCHIINSA MAGAALAA FINFINNEETTI SAGANTAA QORMAATA XUMURA SADARKAA 1FFAA KUTAA 8FFAA BARA 2013/2021

የክፍል ደረጃ	ፈተና የሚሰጥበት ቀን GUYYAA QORMAATNI ITTI KENNAMU			ጊዜ YEROO	የትምህርት አይነት GOSA BARNOOTA
G 8 P S L C E	1	ረቡዕ ROOBII	ሰኔ 23/2013 ዓ.ም WAXABAJJII	ጠዋት 3:00-5:00 WAAREE DURA	ክፍል አንድ አማርኛ እና እንግሊዘኛ AFAAN AMAARAA FI INGLIFFAA
				MORNING 9:00-11:00	PART ONE AMHARIC AND ENGLISH
		WEDNESDAY	JUNE 30/2021 G.C	ከሰዓት 8:00-10:00 WAAREE BOODA	ክፍል ሁለት ሂሳብና ባዮሎጂ HERREEGA FI BAAYOLOOJII
				AFTERNOON 2:00-4:00	PART TWO MATHEMATICS AND BIOLOGY
	2	ሐሙስ KAMISA	ሰኔ 24/2013 ዓ.ም WAXABAJJII 25/2013	ጠዋት 3:00-5:00 WAAREE DURA	ክፍል ሶስት ፊዚክስ እና ኬሚስትሪ FIIZIKSII FI KEEMISTIRII
				ከሰዓት 8:00-11:00 WAAREE BOODA	ክፍል አራት የህብረተሰብ ሳይንስ እና ስነ ዜጋ ስነ ምግባር HAWAASAA FI BLAG
		THURSDAY	JULY 1/2021 G.C	MORNING 9:00-11:00	PART THREE PHYSICS AND CHEMISTRY
				AFTERNOON 2:00-4:00	PART FOUR SOCIAL SCIENCE AND CIVICS AND ETHICAL EDUCATION
	3	አርብ JIMAATA	ሰኔ 25/2013 WAXABAJJII 25/2013	ጠዋት 3:00 -5:00 WAAREE DURA	ክፍል አምስት አፋን ኦሮሞ እና ገዳ AFAAN OROMOO FI GADAA
		FRIDAY	JULY 2/2021 G.C	MORNING 9:00 -11:00	PART FIVE AFAN OROMO AND GADAA

- በፈተና አስፈጻሚነት የተሰማራ የሰው ኃይል መረጃ

ጣቢያ	የጣቢያ ኃላፊ	ሱፐርቫይዘር	ፈታኝ	ድምር
173	173	613	1840	

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትም/ት ቢሮ ለ2013 ዓ.ም የ8ኛ ክፍል አስፈታኝ ት/ቤቶች እና የጣቢያ ብዛት የ8ኛ ክፍል አስፈታኝ ት/ቤቶችና የጣቢያ ብዛት

ተ.ቁ	ክፍለ ከተማ	አስፈታኝ ት/ቤት ብዛት	የፈተና ጣቢያ ብዛት	የክ/ከተማ የግል አስፈታኝ	አጠቃላይ የተማሪ ብዛት
1	አዲስ ከተማ	33	9	1	3535
2	አቃቂ	60	25	1	6844
3	አራዳ	50	10	1	4434
4	ቦሌ	65	14	1	5707
5	ጉለሌ	41	21	1	5292
6	ቂርቆስ	43	13	1	4153
7	ኮልፌ	104	22	1	15126
8	ልደታ	24	9	1	2221
9	ንፋስ ስልክ	108	21	1	11376
10	የካ	72	14	1	7883
11	ለሚ ኩራ	50	12	1	6848
	ድምር	**650**	**170**	**11**	**73419**
	ከሀገር ውጭ		3	0	355
			173		**73774**

ክፍለ ከተማ አስተባባሪዎች ተግባርና ሃላፊነት

1.ስለፈተናው አስፈላጊውን ገለፃ (Orientation) በክፍለ ከተማ ሥር ለተመደቡት የጣቢያ ኃላፊዎች በሙሉ ይሰጣል

2. በክፍለ ከተማው በተካተቱ የፈተና ጣቢያዎች ከፈተና አሰጣጥና ከፈተና ደህንነት ጋር የተይይዙ ችግሮች ሲያጋጥሙ ይፈታል፣ ያማክራል። ችግሮች ከአቅም በላይ ከሆኑ በከተማ አስተዳደሩ ለተቋቋመው የፈተና አስፈጻሚ ግብረ ሃይል ወይም ለቢሮ በማሳወቅ መፍትሄ እንዲፈለግ ያደርጋል

3. ፈተናው በስርዓትና በሰላማዊ መንገድ እንዲካሄድ በአካባቢው ካሉት ፈተናው ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር በትጋት ይሰራል፤

4. ሃላፊነታቸውንና ግዴታቸውን ለማይወጡ የጣቢያ ሀላፊዎች፣ሱፐርቫይዘሮችና ፈታኞች እንዲሁም ር/መምህራንና የፈተና ክፍል ሃላፊዎች ከሚመለከታቸው አካላት ሪፖርት ሲቀርብለት በክ/ከተማ ከሚገኙት ሃላፊዎች ጋር በመነጋገርና ጉዳዩን በማጣራት ከሚቀጥለው ስራ እንዲታገዱና በምትካቸው ሌላ እንዲመደብ ያደርጋል፤

5. ፈተናዎች ከተጠናቀቁ በኋላም ከፈተና ጣቢያ ኃላፊዎች ላይ የመልስ ወረቀት የያዙ ፖስታዎች የታሸጉበትን ሽራ እና የሽራው ቁልፍ የታሸገበትን ፖስታ እንዲሁም ባዶ ሽራዎችንና የተረከቧቸውን ቁልፎች ይረከባል

6 ፈተናን ከትምህርት ቢሮ በመረከብ ለጣቢያዎች ያዘጋጃል

7.ከፈተና በዋላ የተማሪዎች መልስ መስጫ ወረቀትን በወቅቱ ያስረክባሉ

የፈተና ጣቢያ ሀላፊ ተግባርና ኃላፊነት

የፈተና ጣቢያ ኃላፊ ሆኖ የሚመደብ ባለሙያ የፈተናው ሥራ ቁልፍ ሰው እንደመሆኑ መጠን የሚከተለው ተግባርና ኃላፊነት ይኖረዋል።

- በፈተናው አሰጣጥ ሥራ ላይ ለተመደቡ ***ሱፐርቫይዘሮች ፣ ፈታኞችና የፖሊስ አባላት*** ስለፈተና አሰጣጥ ገለፃ (orientation) ይሰጣል፤ የፈተናውን ሥራ ያስተባብራል።
- ***ለዘመኑ ተፈታኞች*** በፈተና አሰጣጥ ወቅት መከበር ስላለባቸው <u>ህጎችና ደንቦች</u>፣ ስለተፈታኞች <u>መብትና ግዳታዎች</u> እንዲሁም <u>የፈተና መልስ ወረቀት አጠቃቀምና አጠቃቀርን</u> በተመለከተ ***በቂ ገለፃ ይሰጣል።***

- በተለያዩ ምክንያቶች አድሚሽን ካርድ ይዘው ባለመምጣታቸው ወደ ፈተና አዳራሽ እንዳይገቡ ለሚከለከሉ መደበኛ ተፈታኞች የትምህርት ቤቱን ርዕሰ መምህር መደበኛ ተማሪዎች ስለመሆናቸው ተገቢውን ማረጋገጫ እንዲሰጥ በማድረግ ወደ ፈተና ክፍል እንዲገቡ ያደርጋል።

- በየዕለቱ የፈተና ክፍለ ጊዜ ፈታኝና ሱፐርቫይዘር በመመደብና በግልፅ በሚታይ ሰሌዳ ላይ በመለጠፍ ሱፐርቫይዘሮችና ፈታኞች እንዲያነቡት ማድረግ አለበት።

- ኃላፊነትና ግዴታቸውን የማይወጡ ሱፐርቫይዘሮችንና ፈታሾችን፣ በእለቱ ከተመደቡበትም ሆነ ከሚቀጥለው ሥራ በማስቆም ወይም በማገድ በምትካቸው ሌላ መመደብ ይችላል። በክፍለ ከተማው ፈተና ክፍል ኃላፊ አማካኝነት ለመለመላቸው አካል የታገዱበትን ምክንያት በመግለፅ ጉዳዩን በፅሁፍ ሪፖርት ያደርጋል
- ***ኃላፊነትና ግዴታቸውን በማይወጡ*** <u>ርዕሳነ መምህራን</u> ላይ በቅድሚያ ***ለማዕከል አስተባባሪው*** ወይም ***ለተቋቋመው ኮማንድ ፖስት*** ወይም ***ለቢሮ*** በማሳወቅ ከተመደቡበትም ሆነ ከሚቀጥለው ሥራ የማስቆም ወይም የማገድና ከሚመለከታቸው ጋር በመነጋገር በምትካቸው ሌላ ማስመደብ ይችላል።

- በጣቢያው ውስጥ ያሉ ተፈታኞችን፣ ፈታኞችን ሱፐርቫይዘሮችንና ፖሊሶችን ያስተባብራል፣ ይመራል፣ ይቆጣጠራል፣ በወቅቱ መፍትሔ በሚሹ ጉዳዮች ላይ አፋጣኝ ውሣኔ ይሰጣል።
- ከአቅም በላይ ከሆነም ከማዕከል አስተባባሪው ጋር በመነጋገር ወይም ባለው የመገናኛ ዘዴ በመጠቀም ከሚመለከተው አካል ጋር በመወያየት ለተከሰተው ችግር አፋጣኝ መፍትሄ በመስጠት ስለአፈፃፀሙ ለቢሮ የጽሑፍ ሪፖርት ያቀርባል።
- ማንኛውም ተፈታኝ ***ፈተናው ከተጀመረ ከ30 ደቂቃ በኋላ ወደ ፈተና ክፍል እንዳይገባ*** ያደርጋል።
- ***ማንኛውም ተፈታኝ ለፈተናው የተፈቀደው የጊዜ ገደብ ሙሉ በሙሉ ሳይጠናቀቅ የተሰጠውን የጥያቄ ወረቀት ይዞ እንዲወጣ የማይፈቀደለት ስለሆነ ይህ ተግባራዊ መደረጉን ይቆጣጠራል።***

- ማየት ለተሳናቸው ተፈታኞች በደንብ ማንበብና መልስ ማጥቆር የሚችሉ የመጀመሪያ ዲግሪ ያላቸው ፈታኞችን መርጦ ይመደባል።
- እነዚህ ፈታኞች ጥያቄ በሚያነቡበት ጊዜ ተዘዋውሮ በመመልከት በትክክል የሚያነቡና የሚያጠቁሩ ካጋጠመው ወዲያውኑ እንዲለወጡ በማድረግ ደግመው እንዲይመደቡም ያደርጋል።

- በተጨማሪም በፈተና አሰጣጥ ሂደት ከተፈታኞች በሱፐርቫይዘሮች አማካይነት የሚቀርቡለትን የፈተና ጥያቄ ዝግጅት ችግሮችን ማስታወሻ ይዞ በአጠቃላይ ሪፖርት ለቢሮ ያቀርባል።
- በፈተና አሰጣጥ ወቅት በቀጥታ ***<u>በፈተና አሰጣጡ ሂደት ላይ ከሚሳተፉ ሰዎች በስተቀር ወደ ፈተና ጣቢያው ቅጥር ግቢ ማንም ሰው እንዳይገባ</u>*** ያደርጋል።

- በፈተና ጣቢያው ውስጥ የተሰራባቸው የመልስ ወረቀቶች በጉዞ ወቅት እንዳይበላሹ ሆነው መታሸጋቸውን ይቆጣጠራል።

- የመልስ ወረቀቶችን የያዙ ፖስታዎች የታሸጉበትን ሸራ እና የሸራው ቁልፍ የታሸገበትን ፖስታ እንዲሁም ባዶ ሸራዎችንና የተረከባቸውን ቁልፍች በሙሉ ለክፍለ ከተማ የፈተና ባለሙያዎች ያስረክባል።

የሱፐርቫይዘር ተግባርና ኃላፊነት

በየፈተና ጣቢያው የተመደቡ ሱፐርቫይዘሮች የየጣቢያ ሀላፊዎች የሚሰጡትን ገለጻ የመከታተል ግዴታና ኃላፊነት ያለባቸው ቢሆንም

ሁሉም የተመደቡ ሱፐርቫይዘሮች በሚወጣው ፕሮግራም መሠረት ***በጣቢያ ኃለፊው በሚሰጠው ገለፃ*** ላይ የመገኘት ግዴታ አለባቸው።

- በዚህ ***ገለፃ ላይ ያልተገኙ ሱፐርቫይዘሮች*** ስም በክፍለ ከተማ የፈተና ክፍል ኃላፊ አማካኝነት ለመልማዩ አካል እንዲደርስ የሚደረግ ሲሆን ***በፈተናው ሥራም ላይ አይሳተፉም።***
- በፕሮግራሙ መሠረት የተመደበ ሱፐርቫይዘር በተመደበበት ጣቢያ ***ፈተናው ከመጀመሩ አንድ ሰዓት ቀደም ብሎ በመገኘት*** ሥራውን ያከናውናል።
- ማንኛውም ***ተፈታኝ <u>ፈተናው ከተጀመረ ከ30 ደቂቃ በኋላ</u> ወደ ፈተና ክፍል ውስጥ እንዳይገባ*** ያደርጋል።
- ማንኛውም ***ተፈታኝ <u>ለፈተናው የተፈቀደው የጊዜ ገደብ ሙሉ በሙሉ ሳይጠናቀቅ</u> የተሰጠውን የጥያቄ ወረቀት ይዞ ከፈተና ክፍል እንዳይወጣ ይቆጣጠራል።***

- በተጨማሪም የጣቢያ ኃላፊው ሁሉንም የመልስ ወረቀቶች ***ተረክቦ***ና ***አደራጅቶ እስኪጨርስ ድረስ የጣቢያ ኃላፊውን በሥራ በመርዳት በጣቢያው መቆየት*** ይኖርበታል።

- በፈተና ሥራ ላይ ***ያረፈደ*** ወይም ***በእያንዳንዱ የፈተና ቀን የጣቢያ ኃላፊው እስኪያሰናብተው በጣቢያው ያልቆየ ሱፐርቫይዘር*** በክፍለ ከተማው ፈተና ክፍል ኃላፊ በኩል ለመለመለው ክፍል የፈፀመው ግድፈት ተገልጾ አስፈላጊው የዕርምት እርምጃ እንደሚወሰድበት ሊያውቅ ይገባል።

- በእያንዳንዱ መፈተኛ ክፍል የዕለቱ የትምህርት ዓይነት ፈተና ሲሰጥ ***የሥም ቁጥጥር ሥራ በአግባቡ መከናወኑን*** ፣ <u>ተፈታኞችም በሚፈተኑት የት/ዓይነት በስም መቆጣጠሪያ ቅፅ ላይ ስማቸውንና መለያ ቁጥራቸውን መጻፋቸውን</u> ማረጋገጥ፣ የመልስ ወረቀቶችን ***ከተፈታኞቹ የምዝገባ ቁጥር አንፃር*** በትክክል በማገናዘብና ***በቅደም ተከተል በማስተካከል***፣ ከፈታኞች በመረከብ ለጣቢያ ኃላፊው ያስረክባል።

ማንኛውም በፈተና ሥራ ላይ ***በሱፐርቫይዘርነት የተመደበ ግለሰብ ተንቀሳቃሽ ስልክ (ሞባይል) ይዞ ወደ ፈተና ክፍል ውስጥ መግባት ወይም በአካባቢው መዘዋወር በጥብቅ የተከለከለ መሆኑን በመገንዘብ ሞባይሉን ሌላ ቦታ አስቀምጦ የመግባት ኃላፊነት/ግዴታ አለበት***

የፈታኝ ተግባርና ኃላፊነት

- በየፈተና ጣቢያው የተመደቡ ፈታኞች የየፈተና ጣቢያ ሀለፊዎች የሚሰጡትን ገለጻ የመከታተል ግዴታና ኃላፊነት ያለባቸው ቢሆንም
- አንድ ፈታኝ በተመደበበት የመፈተኛ ክፍል/አዳራሽ ውስጥ ያለው ጥቁር ሠሌዳ በሚገባ መጽዳቱን፣ የተለጠፉ ትምህርታዊ ቻርቶች፣ ሥዕላዊ መግለጫዎች፣ ፎርሙላዎችና የተለያዩ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ካሉ መነሳታቸውን ወይም መሸፈናቸውን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት።
- ተፈታኞችን በሚፈተኑበት ክፍል/አዳራሽ በር ላይ በምዝገባ ቁጥራቸው ቅደም ተከተል በማሰለፍ እና የምዝገባ ካርድ (Admission Card) በማየት መቀመጫ ያስይዛል።

- በተጨማሪም መፈተኛ ክፍል ውስጥ ከገቡ በኋላ የተፈታኞችን ማንነትና የምዝገባ ቁጥር ያረጋግጣል።
- ተፈታኞች ከእርሳስ፣ ከላጲስ፣ ከመቅረጫና ከማስመሪያ በስተቀር ሌሎች ነገሮችን ማለትም ***ሞባይል፣ ካልኩሌተርና*** የመሳሰሉ ***የኤሌክትሮኒክስ ዕቃዎችን*** ***ወደ ፈተና ክፍል ይዘው እንዳይገቡ*** ይቆጣጠራል።
- በተጨማሪም መፈተኛ ክፍል ውስጥ ከገቡ በኋላ ***የእያንዳንዱን ተፈታኝ ማንነትና የምዝገባ ቁጥር ትክክለኛነት ወይም ተዛማጅነት*** ያረጋግጣል።

- እያንዳንዱ ተፈታኝ የተመዘገበበትን የት/ዓይነት ስለመፈተኑ፤ በተዘጋጀው የመቆጣጠሪያ ቅፅ (Attendance Sheet) ላይ ሰም እና መለያ ቁጥር ይጽፋል ስለመፈተኑም √ ምልክት ያደርጋል

- የፈተና ተሳትፎ መቆጣጠሪያ ቅፅ /Attendance Sheet/ ላይ በየገጹ የተፈተኑ ተማሪዎች ቁጥር ቅጹ በሚፈቅድው ቦታ መቀመጥ አለበት

- ፈተናው ከተጀመረ ከ30 ደቂቃ በኋላ ዘግይተው የሚመጡ ተፈታኞች ወደ ፈተና አዳራሽ አንዳይገቡ ይከለክላል።

- ፈተናው ተጀምሮ አስከሚጠናቀቅ ድረስ ተፈታኞች የቀራቸውን ጊዜ በየ30 ደቂቃው ያስታውሳል።
- ፈተናው እንደተጠናቀቀ የመልስ ወረቀቶችን በምዝገባ ቁጥር ቅደም ተከተል በማስተካከል፤ በተፈታኞች መቆጣጠሪያ ቅፅ (Attendance Sheet) በማገናዘብ ለሱፐርቫይዘሩ ወዲያውኑ ያስረክባል።
- ማንኛውም በፈተና ሥራ ላይ በፈታኝነት የተሰማራ ግለሰብ ተንቀሳቃሽ ስልክ (ሞባይል) ይዞ ወደ ፈተና ክፍል ውስጥ መግባት በጥብቅ የተከለከለ መሆኑን በመገንዘብ ሞባይሉን ሌላ ቦታ አስቀምጦ የመግባት ኃላፊነት/ግዴታ አለበት።

የተፈታኞች መብትና ግዴታ

- ማንኛውም ተፈታኝ **<u>የፈተና ደንብና ሥርዓት</u>** አክባበር እንዲሁም **<u>የመልስ ወረቀት አጠቃቀርና</u>** ተዛማጅ ሁኔታዎችን አስመልክቶ **<u>በሚሰጡ ገለፃዎች ላይ የመሣተፍ ግዴታ አለበት</u>**።

- ተፈታኙ ***በገለፃው ላይ ባለመሳተፉ*** ምክንያት በፈተና አሰጣጥ ዙሪያ ***ለሚያጋጥመው ችግር ኃላፊነቱን ይወስዳል***።

- በመጨረሻም የሰራበትን የመልስ ወረቀት ለፈታኙ በመስጠት የጥያቄ ወረቀቱን ይዞ መውጣት ይችላል

- ማንኛውም ተፈታኝ የፈተና ጥያቄዎቹን መሰራት ከመጀመሩ በፊት በፈተና የመልስ መስጫ ወረቀት ላይ የግል መለያ መረጃዎችን በሙሉ ግልፅ በሆነ ሁኔታ በቅደም ተከተል ጽፍ ማጥቆር ይኖርበታል።
- ማንኛውም ተፈታኝ የራሱን ችሎታና ዕውቀት ተጠቅሞ መሰራት ይጠበቅበታል።
- የሚሠራባቸው የጥያቄና የመልስ መስጫ ወረቀቶች ለሌሎች ተፈታኞች ዕይታ የተጋለጡ እንዳይሆኑ ሸፍኖ መሰራት ይኖርበታል።

- ማንኛውም ተፈታኝ ***ሞባይል፣ ካልኩሌተርና*** የመሳሰሉ ማንኛውንም ዓይነት ***የኤሌክትሮኒክስ ዕቃዎችን ይዞ ወደ ፈተና ክፍል መግባት በጥብቅ የተከለከለ ነው ።***

–

- እያንዳንዱ ተፈታኝ ይህንን አውቆ ***በቅድሚያ አስፈላጊውን ጥንቃቄ ማድረግ አለበት ።***

- ይህንን ***ባለማድረጉ ምክንያት በፈተና አሰጣጥ ዙሪያ ለሚያጋጥመው ችግር ተፈታኙ ራሱ ኃላፊነቱን ይወስዳል።***

- ማንኛውም ተፈታኝ በመፈተን ላይ እያለ ፈተናውን እንዳይሠራ የሚያውኩ ሁኔታዎች ቢያጋጥመው በፈታኙ ሲፈቀደለት ችግሩን በመግለጽ አስፈላጊውን እርዳታ ማግኘት ይችላል። ይሁንና በማንኛውም ምክንያት ለባከነ ጊዜ ተጨማሪ ሰዓት አይፈቀድም።
- ማንኛውም ተፈታኝ ፈተናው ከሚጀመርበት ጊዜ ተኩል ሰዓት /30 ደቂቃ/ ቀደም ብለው ከመፈታኛው ቦታ በመገኘት መቀመጫቸውን መያዝ አለባቸው። ፈተናው ከተጀመረ ከ15 ደቂቃ በኋላ የሚመጣ ተፈታኝ ወደ ፈተናው አዳራሽ መግባት አይፈቀድለትም።
- ማንኛውም ተፈታኝ ፈተናው ተጀምሮ 45 ደቂቃ ሳይሞላ ፈተናውን ሠርቶ ቢያጠናቅቅም እንዲወጣ አይፈቀድለትም። ይሁን እንጂ ፈተናው ከተጀመረ ከ45 ደቂቃ በኋላ ከፈተና አዳራሹ ለመውጣት እንዲፈቀድለት ሲጠይቅ የመልስ ወረቀቱን ለፈታኙ አስረክቦ በጸጥታ እንዲወጣ ይፈቀድለታል።
- ፈተናው ሊጠናቀቅ ከ10 ደቂቃ ያነሰ ጊዜ ሲቀረው የሚጨርስ ተፈታኝ የሁሉም ተፈታኞች የመልስ ወረቀቶች እስኪሰበሰቡና ለፈተናው የተፈቀደው የጊዜ ገደብ አብቅቶ እስኪደወል ድረስ በቦታው ተቀምጦ እንዲቆይ ይደረጋል።

- ፈተናው በሚሰጥበት ጊዜ ማንኛውም ተፈታኝ ትክክለኛ ያልሆነ የተቀደደ ወይም የተበላሸ የፈተና ጥያቄ ጥራዝ ከገጠመው ወይም የተሰጠው የመልስ ወረቀት የተበላሸ ከሆነ ወይም በራሱ እጅ ቢበላሸበት እጁን አንስቶ በመጠየቅ ሲፈቀድለት ሊያስቀይር ይችላል።

- ማየት ለተሳነው ተፈታኝ የፈተናውን ጥያቄዎች የሚያነብለትና የሚሰጣቸውን መልሶች የሚያጠቁርለት ፈታኝ በግሉ እንዲመደብለት ይደረጋል።

- ተፈታኞች ፈተናውን ለመውሰድ የሚችሉት በቅድሚያ ትም/ቤት በተመዘገበበት ጣቢያ እንጂ የፈተና ጣቢያ ቀይረው ሊፈተኑ አይችሉም።

- እያንዳንዱ ተፈታኝ በተዘጋጀው የፈተና ተሳትፎ መቆጣጠሪያ ቅፅ /Attendance Sheet/ በስም መቆጣጠሪያው ላይ የየትምህርት ዐይነቱ የተፈታኙ ስምና መለያ ቁጥር መጻፍ አለበት፤ ተፈታኞች √ ምልክት መፈተናቸውን X ምልክት ደግሞ አለመፈተናቸውን የሚገልጹ ምልክቶች መደረግ አለበት

- Attendance

የመልስ መስጫ ቅጽ ላይ የሚሞሉ መረጃዎችን በተመለከተ

በተማሪዎች አይነት እና በትምህርተ ቤት ይዘታ ኮድ

Student Type	School Type	Code	
Regular	Government	0	1
	Pri/org/Mis/Mos/ Chu	0	2
Night	Government	0	3
	Pri/org/Mis/Mos/ Chu	0	4
Private		0	5

የክፍለ ከተሞች ኮድ

Sub-City	Code	
Addis Ketema	0	1
Akaki kality	0	2
Arada	0	3
Bole	0	4
Gulele	0	5
Kirkos	0	6
Kolfe Keraniyo	0	7
Lideta	0	8
Nifas Silk Lafito	0	9
Yeka	1	0
Lemi Kura	1	1

የመልስ ወረቀት አሞላልና አጠቃቀርን በሚመለከት

- ተፈታኞች የመልስ ወረቀቱን ሲሞሉ የሚፈጽሙት ስህተት ያልተጠበቀ ውጤትን ለማግኘት መንስኤ ሊሆን ስለሚችል ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ አስፈላጊ ነው። እንደምዝገባ ቅጽ ሁሉ የመልስ ወረቀትም የሚነበበው የቅጽ ማንበቢያ መሣሪያ ወይም ማረሚያ መሣሪያ / Opitical Mark Reader/ ነው። ስለዚህ
- ተፈታኞች በፈተና ወቅት መልስ ሲሠሩ ከሳጥኖቹ ሳያልፉ **እድምቀው ማጥቆር** አለባቸው። በደማቁ ያልጠቆሩ ወይም **በከፊል** ብቻ የጠቆሩ የመልስ ወረቀቶች ለማረሚያ ማሽኑ ስለማይነበቡለት ጥራቱ በተጠበቀ **እርሳስ** ብቻ በመጠቀም እድምቆ ማጥቆር አስፈላጊ ነው። **በብዕር** ወይንም **በእስክርብቶ** የተጠቆረ የመልስ ወረቀት ማረሚያ ማሽኑ ስለማያነበው ከእርሳስ ውጪ መጠቀም አጥብቆ የተከለከለ ነው።
- የተሻሸ፣የታጠፈ በእስክርብቶ የተጠቆረ ወይም መጻፍ የተከለከለባቸው ቦታዎች ላይ የተጻፈበት የመልስ ወረቀት የማረሚያ ማሽኑ ማረም ስላማይችል ለተከለከለ ነው።

ADDIS ABABA CITY GOVERNMENT EDUCATION BUREAU

Primary School Leaving Examination Answer Sheet

PRINT

NAME _____ F. NAME _____ G.F. NAME _____

SCHOOL _____ SCHOOL TYPE _____ SUB-CITY _____

INSTRUCTIONS

PRINT YOUR REGISTRATION NUMBER AND SCHOOL CODE IN THE SPACES PROVIDED. THEN MARK THE CORRESPONDING BOX IN THE COLUMN BELOW EACH LETTER OR NUMBER.

MARK LIKE THIS

REGISTRATION NUMBER

SCHOOL CODE

SUB-CITY | SCHOOL TYPE | SCH. NO.

SUBJECT NAME

MARK SUBJECT

Amharic | Afaan Oromoo 1ffaa
Mathematics | Afaan Amhaaraa 2ffaa
Physics | Herrega (AO)
Social Studies | Fiziksii (AO)
Hawaasa (AO)

1	A B C D	21	A B C D	41	A B C D	2	A B C D	22	A B C D	42	A B C D
3	A B C D	23	A B C D	43	A B C D	4	A B C D	24	A B C D	44	A B C D
5	A B C D	25	A B C D	45	A B C D	6	A B C D	26	A B C D	46	A B C D
7	A B C D	27	A B C D	47	A B C D	8	A B C D	28	A B C D	48	A B C D
9	A B C D	29	A B C D	49	A B C D	10	A B C D	30	A B C D	50	A B C D
11	A B C D	31	A B C D	51	A B C D	12	A B C D	32	A B C D	52	A B C D
13	A B C D	33	A B C D	53	A B C D	14	A B C D	34	A B C D	54	A B C D
15	A B C D	35	A B C D	55	A B C D	16	A B C D	36	A B C D	56	A B C D
17	A B C D	37	A B C D	57	A B C D	18	A B C D	38	A B C D	58	A B C D
19	A B C D	39	A B C D	59	A B C D	20	A B C D	40	A B C D	60	A B C D

SUBJECT NAME

MARK SUBJECT

English | Baayoloojii (AO)
Biology | Keemistirii (AO)
Chemistry | BLAG (AO)
Civics | Gadaa

1	A B C D	21	A B C D	41	A B C D	2	A B C D	22	A B C D	42	A B C D
3	A B C D	23	A B C D	43	A B C D	4	A B C D	24	A B C D	44	A B C D
5	A B C D	25	A B C D	45	A B C D	6	A B C D	26	A B C D	46	A B C D
7	A B C D	27	A B C D	47	A B C D	8	A B C D	28	A B C D	48	A B C D
9	A B C D	29	A B C D	49	A B C D	10	A B C D	30	A B C D	50	A B C D
11	A B C D	31	A B C D	51	A B C D	12	A B C D	32	A B C D	52	A B C D
13	A B C D	33	A B C D	53	A B C D	14	A B C D	34	A B C D	54	A B C D
15	A B C D	35	A B C D	55	A B C D	16	A B C D	36	A B C D	56	A B C D
17	A B C D	37	A B C D	57	A B C D	18	A B C D	38	A B C D	58	A B C D
19	A B C D	39	A B C D	59	A B C D	20	A B C D	40	A B C D	60	A B C D

© DRS Data Services Limited [2020]/01151/0920/EQFS

ADDIS ABABA CITY GOVERNMENT EDUCATION BUREAU

Primary School Leaving Examination Answer Sheet

PRINT

NAME _____ F. NAME _____ G.F. NAME _____

SCHOOL _____ SCHOOL TYPE _____ SUB-CITY _____

160920028(40)

INSTRUCTIONS

PRINT YOUR REGISTRATION NUMBER AND SCHOOL CODE IN THE SPACES PROVIDED. THEN MARK THE CORRESPONDING BOX IN THE COLUMN BELOW EACH LETTER OR NUMBER.

MARK LIKE THIS (A) (B) (C) ■ (E)

REGISTRATION NUMBER

SCHOOL CODE

SUB-CITY | SCHOOL TYPE | SCH. NO.

R 9308

SUBJECT
NAME

MARK
SUBJECT

Amharic ☐
Mathematics ☐
Physics ☐
Social Studies ☐
Afaan Oromoo 1ffaa ☐
Afaan Amhaaraa 2ffaa ☐
Herrega (AO) ☐
Fiiziksii (AO) ☐
Hawaasa (AO) ☐

1	[A] [B] [C] [D]	21	[A] [B] [C] [D]	41	[A] [B] [C] [D]
2	[A] [B] [C] [D]	22	[A] [B] [C] [D]	42	[A] [B] [C] [D]

SUBJECT
NAME

MARK
SUBJECT

English ☐
Biology ☐
Chemistry ☐
Civics ☐
Baayoloojii (AO) ☐
Keemistirii (AO) ☐
BLAG (AO) ☐
Gadaa ☐

1	[A] [B] [C] [D]	21	[A] [B] [C] [D]	41	[A] [B] [C] [D]
2	[A] [B] [C] [D]	22	[A] [B] [C] [D]	42	[A] [B] [C] [D]

የመልስ መረቶች የሚካተትባቸው መረጃዎች

የመጀመሪያ ደረጃ ማጠናቀቂያ ክልላዊ ፈተና የመልስ መረቀት የሚከተሉት መረጃዎች በጥንቃቄ ተነብበው መሞላት አለባቸው።

- የእያንዳንዱ ተፈታኝ ስም፣ የአባት ስም እና የአያት ስም በጽሑፍ የሚገለጽበት ክፍት ቦታ /ከተፈቀደው ቦታ ውጭ አለመውጣት/
- የትምህርት ቤቱ ስም የሚጻፍበት ክፍት ቦታ፣ የትምህርት ቤት ይዘታ
- የምዝገባ ቁጥር ተሞልቶ ቁልቁል በትይዩ ያሉ ቁጥሮች የሚጠቆሩባቸው ቦታዎች፣
- የትምህርት ቤቱ መለያ ቁጥር ተሞልቶ ቁልቁል በትይዩ ያሉ ቁጥሮች የሚጠቆሩባቸው ቦታዎች፣
- በእለቱ የሚወሰድ የትምህርት አይነቶች መጥቆር አለባቸው
- ለእያንዳንዱ ጥያቄ በተፈታኝ የተመረጡ መልሶች የሚጠቆሩባቸው ቦታዎች ናቸው።
- ከላይ የተጠቀሱት መረጀዎች በሙሉ ከመግቢያ ካርድ ጋር የሚወሰዱ ናቸው።
- በ ከመግቢያ ካርድ ላይ የስም ሁሄ ግድፈት ቢኖርም በመለስ መስጫ ወረቀት ላይ ትክክለኛው ይጻፍ

ክልላዊ የመጀመሪያ ደረጃ /8ኛ ክፍል/ማጠናቀቂያ ፈተና የሚሰጥባቸው የትምህርት ዓይነቶች

- **በአማርኛ ቋንቋ፡-** አማርኛ ቋንቋ ፣ እንግሊዝኛ ቋንቋ ፣ሂሳብ ፣ባዮሎጂ ፣ፊዚክስ፣ ኬሚስትሪ፣ ሶሻልስተዲ ፣ሥነ ዜጋና ሥነ ምግባር ትምህርት ናቸው፤ (8 የትምህርት ዓይነቶች)
- **በአፋን ኦሮሞ ፡-**አማርኛ ቋንቋ ፣ እንግሊዝኛ ቋንቋ ፣ሂሳብ ፣ባዮሎጂ ፣ፊዚክስ፣ ኬሚስትሪ፣ ሶሻልስተዲ ፣ሥነ ዜጋና ሥነ ምግባር ፣አፋን ኦሮሞ እና ገዳ ትምህርት ናቸው፤(10 የት/ም ዓይነቶች)

- ሁሉም ተፈታኞች ማየት ከተሳናቸው ተፈታኞች በስተቀር ሁሉንም የትምህርት ዓይነቶች የመፈተን ግዴታ አለባቸው። ያልተፈተኗቸው የፈተና ዓይነቶች ካሉ ቀሪ እንደሆኑ ይቆጠራል።
- ማየት የተሳናቸው ተፈታኞች ከፊዚክስ፣ ኬሚስትሪ እና

ሂሳብ ትምህርቶችን በስተቀር የተቀሩትን የት/ም ዓይነቶች መውሰድ አለባቸው

- ማየት ለተሳናቸው ተፈታኞች የሂሳብ፣ የፊዚክስና የኬሚስትሪ ትምህርቶችን እንዲፈተኑ አይገደዱም። ውጤቱም ከሦስት የትምህርት ዓይነቶች ውጪ ላሉ ትምህርት ዓይነቶች ተካፍሎ ይቀመጣል።
- 8ኛ ክፍል ማጠናቀቂያ ክልላዊ ፈተና በምዝገባ ጊዜ ቀርቦ ያልተመዘገበ ተማሪ ፈተናውን እንዲወስዱ አይፈቀድለትም።
- ለ8ኛ ከፍል ክልላዊ ፈተና በመደበኛ ፕሮግራም ተመዝግቦ በፈተና ወቀት ቀርቦ ሳይፈተን ለቀረ ወይም እየተፈተነ እያለ በከፊል የተወ ተማሪ በሚቀጥለው ዓመት በመደበኛ ፕሮግራም ተምሮ ፈተና እንዲፈተን ከሚፈቀድለት በስተቀር ልዩ ፈተና ተዘጋጅቶ አይሰጠውም። ሆኖም አብዛኛውን ፈተና ተፈትኖ በሆነ ችግር ምክንያት አንድ ፈተና ሳይፈተን የቀረ ተማሪ ችግሩ በተጨባጭ መረጃ ተደግፎ ሲቀርብ የሠራበት ፈተና ውጤት በ8 ለአማርኛው በ10 ለአፋን ኦሮሞ የትም/ዓይነቶች ተካፍሎ አማካይ ጥሬ ማርክና ፐርሰንታይል ይወጣለታል።

- የመልስ ወረቀቶች በየትምህርት ቤቱ መሰረት የታሸጉ በአንድ ትምህርት ቤት በርካታ ተማሪዎች ተፈታኞች በመሆናቸው በአንድ ፖስታ ውስጥ ማሸግ ካልተቻለ ከአንድ በላይ በሆነ ፖስታ ማሸግ ይቻላል ፤ነገር ግን ፖስታው ላይ በሚገለጸው መሰረት ከአንድ በላይ ፖስታ መኖሩን በመጻፍ ማሳወቅ ያስፈልጋል

•የማታ ተማሪዎች ያሉበት ትምህርት ቤት የመልስ ወረቀት ከቀኖች ጋር መቀላቀል የለበትም፤የማታ ተማሪዎች የመልስ ወረቀት ለብቻ መታሸግ አለበት

•በየፈተና ዕለት በፈተና መጨረሻ ላይ የተረከበውን መልስ ወረቀቶችን በአግባቡ ቆጥሮ በማሸግ እና በታሸገበት ፖስታ ላይ እንዲጻፉ የሚጠየቀውን መረጃ በሙሉ በመሙላት ለፈተና ማሸጊያ በተፈቀደው ፖስታ ብቻ በማሸግ ያስረክባል፤

- ፖስታው ላይ ያሉ መሞላት ያለባቸው መረጃዎች

Guyyaa_____

- BIROO BARNOOTA BULCHIINSA MAGAALAA FINFINNEE
- IBSA QORUMSA XUMURA BARNOOTA SADARKAA TOKKOFFAA (KUTAA 8FFAA) BARA 2013
- Kutaa Magaalaa:_____
- Maqaa Aanaa:_____
- Maqaa mana Barumsaa:_____
- Itti Gaafatamaa Buufata Qorumsaa :Maqaa_____ Bilbilaa_____
- Akaakuu Barumsaa_____fi _____
- Baay'ina qoratamtoota qorumsa fudhatanii Dhi _____ Dubara_____
- Baay'ina waraqaa deebii poostaa kana keessa jiruu_____
- Nuti, poostaa kana keessatti waraqaaleen deebii bay'inni isaanii _____ ta'e bakka jirrutti tartiibaan lakkaa'amanii poostaatti galchuudhaan yeroo cuqqaalaman arginee mallatteessineerra.

T.L Mallattoo	Maqaa miseensotaa	Dhaabbata/ kutaa hojii bakka bu'an
1	_____	_____ _____
2	_____	_____ _____
3	_____	_____ _____

- Chaappaa Mana Barumsaa

GRADE 8

ADDIS ABABA CITY GOVERNMENT EDUCATION BUREAU

ANSWER SHEET CASE

20_____E.C.

Sub-City_____ Subject_____

School_____

No. of Answer Sheets_____

Package_____ of_____

We, the undersigned hereby certify that this case was sealed in our presence and the information is complete and accurate.

	Name	Position	Signature
1.	_____	(Center Chief)	_____
2.	_____	(Supervisor)	_____
3.	_____	(School Rep.)	_____

Date_____

Tel. 011-1223912

School seal

- SUBCITY
- SUBJECT
- SCHOOL
- NO OF ANSWER SHEETS
- PACKAGE OF
- CENTER CHIEF,SUPERVISOR AND SCHOOL REPRESENTATIVE
- NAME AND SIGNATURE
- በመልስ ወረቀቶችን በያዘ ፖስታ ላይ ሱፐርቫይዘሩ እና የጣቢያ ሃላፊው በተቀመጠላቸው ቦታ ስምና ፊርማቸውን ማስቀመጥ አለባቸው ለፊረሙበትም የመልስ ወረቀት ብዛት እና ጥራት ሃላፊነት ይወስዳሉ፤
- በመልስ ወረቀቶችን በያዘ ፖስታ ውስጥ ከመልስ መስጫ ወረቀት ውጪ ሌላ ወረቀት ቀላቅሎ ማሸግ **አይፈቀድም**፤ ለምሳሌ(የፊተና ተሳትፎ መቆጣጠሪያ ቅፅ /Attendance Sheet/
- የተፈታኞች የስም መቆጣጠሪያ /Attendance Sheet/ የሚታሸገው ለብቻ ነው

- ፈተናው እንደተጠናቀቀ የመልስ ወረቀቶችን መጨማደድና መቀደድ ሳይኖር በጥንቃቄ በማደራጀት በሁለት ቀናት ውስጥ የፈተና ጣቢያ ሀላፊዎች ከክፍለ ከተማ የፈተና ባለሙያዎች ጋር አስፋለጊውን ጥበቃ በማድረግ ወደ ቢሮ የሰረክባሉ፤

የቀጣይ ተግባራት

ተ.ቁ	ተግባራት	የክንውን ጊዜ
1	በፈተና አስተዳደር ዙሪያ ለክፍለ ከተማ አስተባባሪዎች ሥልጠና መስጠት፣	17/10/13
2	ፈተና የያዙ ሽራዎች ወደ ጣቢያ ማሰራጨት	20/10/13
3	የፈተና አሰጣጥ ሥራ ማስተባበር፣	23-25/10/13
4	የፈተና መልስ ወረቀቶች መረከብ፣	26-27/10/13
5	የፈተና መልስ ወረቀቶች ለእርማት ማዘጋጀት፣	1-5/11/2013
6	የተፈታኞች አቴንዳንስ መሙላት፣	6-9/11/13
7	የፈተና መልስ ወረቀቶች ስካኒንግ ማካሄድ፣	6-15/11/13
8	የመልስ ወረቀት ኪኮሬክሽን ማካሄድ፣	10-15/11/13
9	የፈተና ውጤት ምስክር ወረቀት ማሳተምና ለክ/ከተሞች ማሰራጨት፣	ከ15/11/13 በኋላ

አመሰግናለሁ!